# ግጥምጥሞች

አብርሃም በየነ

ወጣት በፍቅር እሳት ተቃጥሎ ነደደ
ሲሉት እየቀና
ሮጦ ለመድረስ ልጅነት ከርጅና
ከነፈ ነጎደ በጊዜ ጎዳና
ግን አርጅቶ ሲያየው ፍቅር እያበደ
የሚስመው ጥፍቶ ከንፈር ቆረፈደ።

*   *   *

ፍክክ ፍንድቅ ያለች ፍንድሽ ጽጌረዳ
በልቤ ቀብሬ በፍቅር ቤት ጓዳ
እንዳንገቷ መስቀል አስራኝ በማተቧ
ስትበላው እንድትኖር ልቤን እንደ ልባ
ቃል ኪዳኔን ታጥቆት ሽንጥና ወገቧ
ካንጀቷ እውላለሁ መቀነቷን ሆኘ
ማር ዘነብ ከንፈሯን ልቤ እየጎበኘ።

*   *   *

በምእራብ በምስራቅ የውቀት ጥበብ ጮራ
እድገት ስልጣኔ ነጻነት ሲያበራ
በዘር መድሎ ቀንበር ላለን በጭቆና
አልወጣችም ጸሃይ ጨለማ ነው ገና።

*   *   *

እንደ ዘመነኛው ሁሉም እንደ ቻቱ
ዘሮች ካፈር ወድቀው ቢሞቱ ቢሞቱ
ምነው አልሆን አለ ፍሬአማ መሬቱ?

*   *   *

የጠገዴ ነገር አጅሬ ጃኖራ
የጸለምትም ነገር ሰሜን ጃናሞራ
የወልቃይት ነገር ይቅር አይወራ
መሬቱን ሲነጠቅ ለሰሚው ነው ግራ
አዝማሪ ቤት ዘግቶ ከቦ በወበራ
ጎንደር አለቀሰ በፈረሱ ጭራ።

*   *   *

የአድዋ ባንዶች ሞራል ያጡት
አምቦን አድቅቀው ቀጥቀጡት
ጎንደርንም ቀጡት- ወሎን በበለጠ
ምን ቀረው ብለው ነው
ሰው የጁን ከሰጠ?

*   *   *

እርጅና የሚሉት የሞት ታናሽ ወንድም
ባገር ጉዳይ ዙሪያ ሲያልፍና ሲያገድም
በሰአት እሩጫ ገጥሞን እሽቅድድም
የማታ የማታ ወንድሙን ካልጠራ
ማቸነፉን እንጃ በእድሜ እያስፈራራ።

*   *   *

**በፍትሁ መድሎ ጭቆና
ባወጣው ህግ ካቴና
ትንፍሽ እንዳይል ህዝብ አዳሙ
የአፍ ድጁ እንዳይከፈት -ዝሙ
ከንፈር ዘብ መቆሙ
ለአንደበት ሲሆን ልጓሙ
ነገር አለሙ ይደንቃል
 አፍ ተለጉሞ ተጨንቆ
ጥርስ ከፍቶት ይስቃል።**

*   *

**የሰውን ክብር አንበርክኮ
የውርደት እከክ አሳክኮ
ስብእናውን የገደለ
እንደ ማጣት ማንም የለ።**

*  *  *

**ስሩ እንደ ጠነኀ እሾኩ እንደ ግራር
ቅጥነቱ እንደ ጅማት ቅኝቱ እንደ ክራር
የማእጠኑ-ሽቱ ጥእምናው የከርቤ
ፍቅርሽ ቤተ-መቅደስ መሆኑን ታዝቤ
ገዝቸ ፈታሁት ቄስ ሆኘ በልቤ።**

**   **  **

**የሚበላው አጥቶ ህዝብ አዳም ሲቸገር
ህንጻ ቢገነባ ድንጊያ ቢደረደር
መንገድ ቢዘረጋ አስፋልትና ጠጠር
ፎቁ ቢያንጸባርቅ ቢንጣለል አስፋልቱ
ከሰው ተራ ወቶ ሰው ከሰውነቱ
ዘውድ ለደፋ ህዝብ በርሃብ ንግስና
ምንድን ነው ትርጉሙ የእድገት ብልጽግና?**

**አብርሃም በየነ**

happy new year